

# እናቴ ኢትዮጵያ

ውዲቷ ኢትዮጵያ
እርጥብ፣ እሸት ገላ
ዳገቱ፣ ሸለቆው
ወይነ ደጋ፣ ቆላ
ራስ ዳሽን ተራራው
ዳሞ ዘገሊላ…

እልም ያለው ጫካ
ጫፋፉና ሳር ሜዳ
ቃጠሎና ሓሩር
ደረቅ ምድረ-በዳ
ፒያሳና መርካቶ
ጊዮረጊስ አራዳ…

ወደ ዓይኔ እየመጣ
የቀን ሕልም ቀትር
የቁም ቅዠት ሆኖ
ሌት ተቀን ዘወትር
ይጐሻሽመኛል
የትዝታ ብትር!

እናቴ ኢትዮጵያ
ውዲቷ ሃገሬ
ጣፋጪቱ ጥንቅሽ፣
አገዳ፣ ሸንኮሬ
ገራገር፣ ባላገር
እትብቴና ዘሬ…

የተወለድኩበት
ያደግኩበት ምድር
በዓይኔ ድቅን ብሎ
ትዝ ባለኝ ቁጥር
ዕንባዬ ያንቀኛል፣
አወይ ያገር ፍቅር!

ግን ችግር መጣና
ከባዱ መከራ
ስደት ወደሚሉት
ዕሬቱ፣ መራራ
ቢሄዱት፣ ቢጓዙት
የማያልቅ ተራራ…

ግራ-ቀኙ ጠፍቶኝ
ማደርያየን ስሻ
በገደላ-ገደል፣
በዳዋና ጥሻ
ያንከራትተኛል
እንደ ዓበደ ውሻ!

እናቴ ኢትዮጵያ
ሕልሜና ሓሳቤ
ብበላም፣ ባልበላም
ጠግቤ፣ ተርቤ
ናፍቆትሽ ዘልዓለም
አይጠፋም ከልቤ…

ዘወትር በችግር
መጐሳቆልሽ
አላይም ያውልሽ
ኮቴን ላልብስሽ
ቆዳየን ገፍፌ
ስጋየን ላብላሽ…

ተርበሽ፣ ታርዘሽ
ማየት እጠላለሁ
በቁሜ፣ በውኔ
በሕይወቴ እስካለሁ
ዓቅሜ የቻለውን
ላደርግ እምላለሁ!

የዓጋሙ፣ የቀጋው፣
የአደዩ ሽቶ
ብከብር፣ ብከስርም
ሱፍ ሆነ ቡትቶ፣
እናቴ ኢትዮጵያ
አልረሳሽም ከቶ!

ኢትዮጵያ ሃገሬ
ዓይብ፣ ማርና ጭኮ
ጥልፍ፣ ነጠላ፣ ጋቢ፣
ድርብ-ርብ ብልኮ
ስደቱ ነው እንጂ
አልካድኩሽም እኮ!

ገ/ኢ. ጐርፉ።